# “እንደገና” – በሕዳሴው ጎዳና

**ታሪኩ ፈለቀ (ከቀራንዮ)**

“በህዳሴው ግድብ ላይ አተኩሮ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የተላለፈው ‘እንደገና’ የተባለ ዘጋቢ ፊልም፤ ኢትዮጵያዊያን በየዘመኑ ያስመዘገቧቸው አኩሪ ታሪካዊ ድሎች ባለቤት ቢሆኑም፤ በአሁኑ ዘመን ሀገራችን የዓለም የድህነትና የረሃብ ተምሳሌት በመሆን የምትታወቅ ሲሆን፤ ትውልዱ ይህን አሳፋሪ የሀገራችንን ገጽታ የመቀየር ታሪካዊ ዕዳ ያለበት መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡”

ይህ አባባል በቅርቡ በአይጋ ፎረም ድረ -ገጽ አንድ ፀሐፊ “እንደገና” በተሰኘው ዘጋቢ ፊልም ላይ የሰጡት አስተያየት ነው፡፡ እርግጥም ይህ አስተያየት የፊልሙን ትክክለኛ ይዘት የሚያመላክት ነው ማለት ይቻላል፡፡ አዎ! ዘጋቢ ፊልሙ አበው በቀደምት ታሪካቸው ያስመዘገቧቸው አብነታዊ ታሪኮች መኖራቸውን ከማተት ባሻገር፣ የያኔውን የስልጣኔና የቀደምትነት ዘመናችንን ያስታውሰናል፡፡ ይህ ትውልድም የያኔውን ዘመን ታሪክ የኋሊት እያሰበ ፣ በህዳሴው ጉዞ በዓለም ፊት የሚታወቅበትን የድህነትና የረሃብ ተጠቃሽ ማንነቱን መቀየር እንዳለበት የሚያስተምር ነው፡፡

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አሁን ካለበት “እሱነቱ” መላቀቅና መለወጥ አይፈልግም ተብሎ አይታሰብም፡፡ የቀደምት አበውንና እመውን የስልጣኔ ማንነት እየተመለከተ፣ የሀገሩን የድህነትና የኋላ ቀርነት ግርዶሽን በመቅደድ ወደ አዲስ ማንነቱ ተቀይሮ ለመታደስ የማይፈልግ ዜጋ አለ ብሎ መገመትም የዋህነት ነው፡፡ ‘ትላንት በስልጣኔ ማማ ላይ የነበረች ሀገሬ፣ ዛሬ በእኔ ትውልድ እንደምን የረሃብ ተምሳሌት ሆና ትጠቀሳለች?’ በሚል ቁጭትም፤ የነገ “እሱነቱን” እውን ለማድረግ መታተሩ የግድ መሆኑ አይቀርም፡፡ ታዲያ ትውልዱ ይህን ለመከወን የተመቻቸ ሁኔታ ያሻዋል፡፡

በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ደግሞ በልማታዊውና በዴሞክራሲያዊው መንግስት አማካኝነት እንደገና ወደ ነበርንበት የስልጣኔ በር ለመዝለቅ የሕዳሴ መንገድ ተጀምሯል፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ወደዚህ በር የሚደረገው ቁርጠኛ ጉዞ አንድ ማሳያ ነው ማለት

ይቻላል፡፡ እናም ዘጋቢ ፊልሙ በግልጽ እንዳመላከተው፤ ትውልዱ ወደ ትናንት "እሱነቱ" ለመመለስ ታሪካዊ ሃላፊነት አለበት፡፡

እንግዲህ በ"እንደገና" ፊልም የቀረበው ታላቅ እና ሀገርን ወደ ተሻለ ህይወት የመለወጥ አደራ ቁም ነገር ይኸው ነው፡፡ ሆኖም አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን የማይመስሉ "ኢትዮጵያዊያን" ‹ለምን እንደገና ወደ ጥንታዊ የስልጣኔ ማንነታችን ተመልሰን እናድጋለን › ይሁን ወይም ሌላ ውሉ በማይታወቅ ምክንያት አንዳንድ ጋዜጦች ለፊልሙ ያልተገባ ስያሜ በመስጠት፤ ታሪኩን ለመቀየር በተነሳው ትውልድ ሞራል ላይ ውኃ ለመቸለስ መሯሯጣቸው በእጅጉ አሳዛኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

እርግጥ በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ጨለምተኞች (Pesimists) መኖራቸው አይቀርም፡፡ ይሁንና እነዚህ "ጨለምተኞች" ሀገራዊ ጥቅም በሆነ ጉዳይ ላይ አብዛኛውን ጊዜ ድጋፍ የሚያሰሙ ናቸው፡፡ የእኛዎቹ ጉዶች ግን እንዲህ አይደሉም፡፡ ምኞታቸው ለዘለዓለም በምጽዋትና በተረጂነት እንድኖር በመሆኑ፤ አንድ ተግባር የእነርሱን የጨለማ ዘፈን እስካሳካ ድረስ ፤በጥላቻ ታውረው ከማላዘን ወደ ኋላ አይሉም፡፡ ከዚህ ማንነታቸው በመነሳትም "እንደገና " በተሰኘው ዘጋቢ ፊልም ላይ በየግል ሚዲያው ያልለጠፉት የጽሑፍ ዓይነት አለ ለማለት አይቻልም፡፡

መቼም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ የሀገሬ ሰው ነውና፤ 'ሚዲያ የሀገር ሕዳሴ ማሳለጫ መሆኑ ቀርቶ፣ የዕድገት መጎተቻ መሳሪያ ሆኖ ስለምን ልማትን የማይሹ ጨለምተኛ ወገኖች መፈንጫ ይሆናል' የሚል ጥያቄን በውስጡ ማንሳቱ የሚቀር አይመስለኝም፡፡ አዎ! ጥያቄው ማንነቱን ለማደስና ስሙን ለመቀየር ጽኑ ፍላጎት ካለው ሀገር ወዳድ ቀናዒ ዜጋ ህሊና ውስጥ አግባብነት አለው፡፡

ይሁንና ማህበራዊ ኃላፊነት የማይሰማቸው አንዳንድ የግል ሚዲያዎች ላይ የሚያላዝኑና መንግስትን ያጥላሉ የሚመስላቸው አንዳንድ ግለሰቦች በነገው በሀገሪቱ ህልውና ላይ በማሴር 'ለምን እናድጋለን?' እያሉ ፤ፀረ - ኢትዮጵያ እኩይ ዓላማቸውን እያራመዱ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሰሞኑን ለንባብ በበቃው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ከርዕሰ አንቀጹ ፊት ለፊት በሚገኝ ቦታ ላይ " 'እንደገና' መብሰል የቀረው ዘጋቢ ፊልም" በሚል ርዕሰ በውሸት (በብዕር) ስም የቀረበ 'አንባቢ ላከልን' ዓይነት ዘገባ ተጠቃሽ ነው፡፡

በቅድሚያ በዩሐንስ ሰ. አሊያም በርዕሰ አንቀጽ ፀሐፊው መጠናቀሩን አፍ አውጥቶ ወደ ሚናገረው ደብዳቤ ተብዬ ከመዝለቄ በፊት፤ ከርዕሰ አንቀፁ ፊት ለፊት ስለሚገኘው የጋዜጣው ክፍል (Op-ed Section) ጽሑፎች ጥቂት ለማለት ወደድኩ፡፡ ይህ ክፍል አልፎ፣ አልፎ የጋዜጣው እውነተኛ ርዕሰ አንቀጽ ሲመስል፤ ብዙውን ጊዜ ግን ከርዕሰ አንቀጹ የተረፉ ቅንጭብጫቢ "ጥላቻዎች" የሚዘረግፉበት ቦታ ነው፡፡

ምናልባትም በቦታው ላይ የሚሰፍሩትና ተላኩልን የሚባሉት "ዘገባዎች" ከርዕሰ አንቀጹ ጋር ያላቸው ልዩነት ምንም ሊባል የሚችል ነው፡፡ በአጭር ቋንቋ በዚህ ክፍል ላይ የሚሰፍሩት "ጽሑፎች" በግጥምም ይሁን በአስተያየት መልክ ይቅረቡ ዋናው መመዘኛቸው "ምን ያህል የርዕሰ አንቀጹ ደቀ - መዝሙር ሆነዋል?" እየተባሉ የሚሰደሩ ይመስላል፡፡ እናም ይህ ቦታ በጋዜጣው ውስጥ የሚገኙ ጥቂት "ጨለምተኞች" መጋለቢያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

እንግዲህ በዚህ ክፍል ነው - "እንደገና" የተሰኘው ዘጋቢ ፊልም በእነዚህ ወገኖች "ህንጻ ስላሴ" በሚል የብዕር ስም የተብጠለጠለው፡፡ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ 'ለምን ፊልሙን አወገዙት?' የሚል ያልበሰለ ተራ ሙግት ውስጥ ለመግባት ፍላጎት የለኝም፡፡ ምክንያቱም ዜጋም ሆነ ጋዜጠኛ ባሻው ጉይ ላይ የመሰለውን አስተያየት የመስጠት ህገ - መንግስታዊ መብት እንዳለው ስለምነገዘብ ነው፡፡ ይሁንና 'የውግዘቱ' መነሻና ትክክለኛነት ‹እውን ዘጋቢ ፊልሙ መብሰል ቀርቶት ነው ወይስ ከጭፍን የጥላቻ ስሜት የመነጨ ?› ከሚል ሃቅ አኳያ መመልከቱ፤ የጨለማው ዘማሪ የሆኑ "ፀሐፍት" ትብዬዎችን ፀረ - ሀገራዊ ወልጋዳ እሳቤን የአደባባይ ፀሐይ እንዲሞቀው ያደርጋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

እስቲ በመጀመሪያ ከርዕሱ እንነሳ፡፡ አንድ ዘጋቢ ፊልም " በስሏል" ወይም "አልበሰለም" የሚል ስያሜ የሚሰጠው ስክሪፕቱ (ጽሑፉ) ከሚያነሳቸው ወሳኝ ጭብጦች እንዲሁም ከቀረጻ ቴክኒኮች አኳያ መሆኑ ይታመናል፡፡ እርግጥ በርካታ የዘጋቢ ፊልም ዓይነቶች ቢኖሩም፤ በሁሉም ዓይነቶች ውስጥ ግን ቀዳሚ ስፍራውን የሚይዘው ፊልሙ የሚያስተላልፈው መልዕክት (ጭብጥ) ነው፡፡ የቀረጻው አግባቦችም መልዕክቱን በማጉላት ረገድ የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ፡፡ የአዲስ አድማሱ "ጨለምተኛ" አስተያየት ሰጪ ግን፤ ይህን መሰረታዊ ጉዳይ ጭራሹንም ሰምተው የሚያውቁ አይደሉም፡፡

እርግጥ በማንኛውም የጋዜጠኝነት ስራ ውስጥ "ሙሉ ለሙሉ ትክክለኛነት" የሚባል ነገር ላይጠበቅ ይችላል፡፡ ሆኖም ፊልሙ ቀደም ሲል ከጠቀስኳቸው መሰረታዊ ጉዳዮች አንጻር ተገቢውን መልዕክት ያስተላለፈ ነው፡፡ "እንደገና " የተሰኘው ዘጋቢ ፊልም የትላንት ማንነታችንን ታሪክ እያጣቀሰ፣ የነገ "ሰውነታችንን" ለመተንበይ የሞከረና አዲሱ ትውልድም ቀዳሚውን የሀገራችንን የስልጣኔ ተጠቃሽነት ዳግም የማምጣት የታሪክ ባለ ዕዳ ጭብጥን የያዘ ነው፡፡ ጭብጡን ለማጉላት የተጠቀመባቸው የቀረጻ ዘዴዎችም የተዋጣለት የሚባል ለመሆኑ ከሙያ አንጻር መናገር ይቻላል፡፡ይሁንና በጋዜጣው የጥላቻ ዜመኞች ፊልሙ "መብሰል የቀረው" የሚል ርዕስ ለምን እንደተሰጠው ለማንም ግልጽ ግልፅ ሊሆን አይችልም፡፡

አንድ "ፀሐፊ ነኝ" ባይ ስለሚፅፈው ጉዳይ ዕውቀት ከሌለው ጠይቆ መረዳት ይኖርበታል፡፡ ተከድኖ እሳት ላይ እንደተጣደ ብረት ድስት ውስጡ በጥላቻ ስሜት ስለታፈነ ብቻ፤ ደስ ያለውን ነገር ሁሉ በመገንፈል መወርወር ያለበት አይመስለኝም፡፡ እውነታን ሳያውቁ በእውር ድንበሩ መንግስትን ለማጥላላት ሲባል በዘፈቀደ የሚገለጹ አባባሎች ትዝብት ላይ የሚጥሉ ከመሆናቸውም ባሻገር፣ ተዓማኒነትንም የሚያሳጡ ናቸው፡፡

ለመሆኑ ለአዲስ አድማሳውያን "ጥላሸት ቀቢዎች" እያንዳንዱ ዘገባ የጥላቻ ጩኸት ካልታከለበት በስተቀር "መብሰል ይቀረዋል" ማለት ነውን? - ዳሩ ግን፤ በማንኛውም ሙያ ውስጥ አንድ ነገር የተዋጣለት (የበሰለ) አሊያም ያልተዋጣለት (ያልበሰለ) ለመባል፤ ሙያው ከሚጠይቀው መለኪያ አኳያ የሚመዘን መሆኑን መገንዘብ በደፈናው ከመዘላበድ እንደሚያድን እነዚህ ወገኖች ማወቅ ያለባቸው ይመስለኛል፡፡

መቼም አንድን ጉዳይ በቀናነት መመልከት የማይወድ ግለሰብ፤ ምንም ዓይነት በጎ ነገር ቢመለከት በውስጡ የሚርመሰመሰው ስሜት "እርሱነቱን" የሚያሳብቅ ነው፡፡ ዘጋቢ ፊልሙን "መብሰል የቀረው" ያሉት ሰውዬም የዚሁ እውነታ ሁነኛ መገለጫ ናቸው፡፡ በጽሑፋቸው መግቢያ አካባቢ "... እያየሁት አዘንኩ፡፡ ... እያዘንኩ አየሁት" በማለት አስገራሚውን የደፈና ማውገዝ የፖለቲካ ላንቲካቸውን ሊገጥሙብን ሞክረዋል፡፡

ታዲያ ይህን አባባል ስመለከት 'ምናልባት ይህን የጥላቻ የስንኝ እንጉርጉሮ የቋጠረው ገጣሚ ይሆን እንዴ ?› ማለቴ ግን አልቀረም፡፡ ግና "ፀሐፊው" ገጣሚ ይሁን

ሌላ፣ ቁም ነገሩ ፅሑፉ ገና ከጅምሩ ፊልሙን በጨለማ ጃኖ ተጀቡኖ ለማየት የፈለገ በመሆኑ የግለሰቡን ማንነት ዝማሜ በገሃድ ከማስረዳቱ ላይ ነው፡፡ እርግጥም "ፀሐፊው" በፀረ - ሀገር አፍራሽ ተልዕኮ ላይ የተሰለፉ ስለመሆናቸው ቀጣዩን ዘለላ ሐረግ ጽሑፋቸውን መመልከቱ በቂ ምላሽ የሚሰጥ ይመስለኛል፡፡

የጨለማው አንጎራጓሪ ሰውዬ "የዘጋቢ ፊልሙ ጭብጥ ህዳሴውን ከማብሰር ዘሎ፣ የትናንት ማንነታችንን ያሳየ ነበር ማለት ይቻግራል...፡፡" ይላሉ። ግና ‹እንዴት?› ለሚለው ጥያቄ ግለሰቡ ምላሽ የላቸውም፡፡ ምክንያቱም አስተያየቱ የቀረበው ስሜትን እንጂ ዕውቀትን ተመርኩዞ ባለመሆኑ ነው፡፡ ይህ የግለሰቡ አባባል ጭብጥ ወይም ማዕከላዊ ሃሳብ (Cetnteral idea) እየተባለ ስለሚጠራው ጉዳይ ምንም ነገር የማያውቁ ከመሆኑም በላይ፣ 'ፊልሙ ማሳየት ያለበት ስለ ትናንት እንጂ ለምን ዛሬ መንግስት ስለሚያከናውናቸው በጎ ነገሮች ያነሳል?' የሚል አንድምታ ያለው "ቀሺም" የማጥላላት አመክንዩ ከመሆን የዘለለ አይደለም፡፡

ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት፣ የዘጋቢ ፊልሙ ጭብጥ የትናንት "እኛነታችንን" ለማምጣት፣ የዛሬው ትውልድ በተቀደደለት ምቹ የህዳሴ ቦይ እንደ ጅረት እየፈሰሰ ማንነታችንን የመቀየር ኃላፊነት እንዳለበት የሚያመላክት ነው፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ ማዕከላዊ ሃሳብ ይዘት አሰራር ውስጥ፣ ተመራጩ አካሄድ የትናንት ማንነትን በቂ በሆነ መልክ በማሳየት፣ ተፈላጊውና አሁን መሆን ያለበትን ትዕይንት ማጉላት ደግሞ መልዕክቱ ግቡን እንዲመታ ያደርጋል፡፡

ፊልሙ ገቢራዊ ያደረገውም ይህንን በመስኩ ምሁራን የሚመከር አካሄድን ነው፡፡ ስለ ፊልም አሰራር ምንም ዓይነት ግንዛቤ ሳይኖራቸው በደመ - ነፍስ ተቃርኖ ታውረው ወረቀትና ቀለም ስላላቸው ብቻ የለቀለቁት "የጨለማው ሰው"፣ይህን ነባራዊ ሃቅ እንደ ትምህርት መውሰድ ይኖርባቸዋል ባይ ነኝ፡፡

ዳሩ ግን ግለሰቡ በዚሁ ጽሑፋቸው ላይ "...ፊልሙ ላወቀና ለነቃ ሰው አይመጥንም" እስከማለት የደረሱ አላዋቂ በመሆናቸው "ሚጢጢ" ዕውቀታቸውን ለማደስ የሚፈልጉ አይመስሉም፡፡ በተራ የሰላምታ ደብዳቤ ላይ በግልጽ የሚታወቅ "ጭብጥ" የሚባል ፍሬ ነገርን መረዳት የተሳናቸው ፀሐፊ ተብዬው ፣ በምን ዓይነት የዕውቀት ስሌት "ያወቁና የነቁ " እንደሆኑ ለዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ግልጽ ባይሆንም፣ ከአባባላቸው ግን አንድ

እውነታን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸውም የተቃውሞው ጎራ አታሞ ደላቂ ሆኖ በስሜት እየተነዳ በሀገርና በህዝብ ጥቅም ላይ ሳይቀር በጥላቻ የሚያቀነቅን ሰው፣ 'ከእኔ ወዲያ ላሳር አዋቂ' ባይ መሆኑን ነው፡፡

ይሁን እንጂ፤ "ለጥሩ ዕቃ ማስታወቂያ አያስፈልገውም" እንደሚባለው፣ የግለሰቡ አገላለጽ ለራስ የተሰጠ ምስክርነት ከመሆን ባለፈ አላዋቂነትን አስቀድሞ በመከላከል ላይ ያተኮረ ትንሽዬ "ትወና " መሆኑ ነው፡፡ ሆኖም በሰውዬው ዕውቀት አጠርነት የተገነቡት ቃላት እንደ ባዶ ገረወይና እየተንኳኩ የአንባቢያቸውን ጆሮ ከማደንቆር ውጪ "ሙያዊ ምች" የመታቸው መሆናቸውን የሚሸሽጉ አይደሉም - ማን ነበር 'አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል' ያለው? ...

ታዲያ እዚህ ላይ አንድ ታላቅ እውነትን ማንሳት የግድ ይለኛል፡፡ይኸውም ምንም እንኳን ግለሰቡ "... ፊልሙ ለምን አሁን ያለው መንግስት ያከናወናቸውን በጎ ተግባር ያወሳል?" የሚል አንድምታ ያለው ፍጹማዊ ጥላቻቸውን ለማንጸባረቅ ቢሞክሩም፤ የኢፌዴሪ መንግስት ግን ሀገሪቱን "ሕዳሴ" በተሰኘ ፈጣን የዕድገት እመርታ ባቡር ውስጥ ማስገባቱን ነው፡፡ አዎ! እርሳቸው ያሻቸውን ቢደሰኩሩም፣ ልማታዊው መንግስት ከህዝቡ ጋር ተቀናጅቶ የሀገሪቱን ሕዳሴ ለማረጋገጥ ደፋ ቀና እያለ ነው፡፡

ይህ ዓለም ያወቀው ሃቅ ነው - ሰውዬው ለማየት ቢፈልጉም፣ ባይፈልጉም፡፡ እርሳቸው የሀገሪቱ የሕዳሴ ጅማሮ በ "እንደገና" ፊልም ላይ በመነገሩ ምክንያት የወረቀት ላይ አንበሳ ሆነው 'ያዙኝ፣ ልቀቁኝ" ስላሉ የሚቀየርና የሚተው አይደለም፡፡ እናም ጥላቻን በምርኩዝነት በመጠቀም በሚነዛ የማደናገሪያ ጩኸት ተጨባጭ ተግባራዊ ዕውነታን መሰረዝና መደለዝ የማይቻል መሆኑን መገንዘቡ ቢያንስ የአላዋቂነት ግርዶሽን እንደሚገፍ ማወቅ ይገባል፡፡

ግለሰቡ የማያውቁትን ነገር "አራምባና ቆቦ" እየረገጡ በዘጋቢ ፊልሙ ዙሪያ የሰጡት አስተያየት በእጅጉ አስገራሚ ነው፡፡ ሰውዬው ቀደም ሲል ከጠቀስኩት " ከእኔ ወዲያ ..." ጨለምተኛ እሳቤያቸው እንዲሁም ከ"ጭብጥ" አላዋቂነታቸው በዘለለ፤ ስለ ዘጋቢ ፊልም አሰራር እንጥፍጣፊ ዕውቀት የላቸውም፡፡ ‹እኔ የማውቃቸው ሰዎች እያሉ እንዴት አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ስለ ሀገሩ አስተያየት ይሰጣል?› የሚል የደነዘዘ

ሃሳባቸውን “ፊልሙ  መብሰል ይቀረዋል” ለሚል ማስረጃ አልቦ ንትረካቸው በማጀቢያነት ተጠቅመውበታል፡፡

ግለሰቡ “ዝም አይነቅዝም”  የሚለውን ሀገራዊ ብሂል የሚያውቁት አይመስሉም፡፡ ይህ ይትብሃል አንድ ሰው በማያውቀው ጉዳይ አስተያየት ከሚሰጥ ቢያንስ “ዝም” ማለት ይጠቀመዋል የሚል ትርጓሜ  ያለው ቢሆንም፤ የጥላቻ አንጎራጓሪ አዝማሪው  ታንኳ ግን ከዚህ ተቀባይነት  ካለው አባባል በተቃራኒው የሚቀዝፍ ነው፡፡ በመሆኑም ‘አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ስለ ሀገሩ ለምን አስተያየት ይሰጣል?’ የሚለው የግለሰቡ የአግድሞሽ አመለካከትን የሙጥኝ ያለው ታንኳ  ቀዘፋ፤ ከሁለት አላዋቂነት ስህተቶች የመነጨ  ነው፡፡ አንደኛው የዘጋቢ ፊልም  አሰራርን  ካለማወቅ ሲሆን፤  ሁለተኛው ደግሞ በሙያው ላይ ላለው ዓለም አቀፋዊ አካሄድ ባይተዋር መሆን ነው፡፡

በቅድሚያ በአንድ ዘጋቢ ፊልም የሥራ ሂደት ውስጥ ‘ሊጠየቅ የሚገባው ሰው ማነው?’ የሚል ጥያቄ ፊልሙን ለማዘጋጀት በሚደረገው ጥናት ውስጥ የሚመለስ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ ተጠያቂዎቹ  ግለሰቦች የሚመረጡትም የጭብጡን ግብ ከማሳካት አኳያ ነው፡፡ ደጋግሜ   እንደገለጽኩት የጭብጡ   ማዕከላዊ መልዕክት፤ የትናንት የስልጣኔ ማንነታችንን ዛሬ ላይ በተጀመረው  የህዳሴ ጎዳና እናምጣው የሚል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የሕዳሴው  ተዋንያን ስለ ሀገራቸው የሚሰማቸውን ስሜት  በማጉላት መጠየቁ  ተገቢነቱ አጠያያቂ አይሆንም፡፡

ግቡ የሀገራችንን  ያለፉ ዘመናትን የስልጣኔ  ታሪክንና ሥነ - ህንጻን  ማስተዋወቅ አይደለም፡፡   በመሆኑም   የኪነ - ህንፃ ባለሙያዎች   የግድ አስተያየት መስጠት ይኖርባቸዋል የሚል አመክንዮ  ሊመጣ አይችልም፡፡የፊልሙ ግብ የትላንት ስልጣኔያችንን ጠቅሶ፣   በቁጭት   ለዛሬው ህዳሴያችን ይበልጥ እንድነሳሳ የሚያደርግ   በመሆኑ፤ የማንኛውንም ዜጋ ቀናዒ  አስተያየት በግብዓትነት ሊያዝ ይችላል፡፡

በዘጋቢ ፊልሙ ላይ ኃይሌ ገብረስላሴም ሆኑ ሌሎች አስተያየት ሰጪዎች የተካተቱም ከዚህ እሳቤ  በመነሳት ይመስለኛል፡፡ ስለሆነም አትሌት ኃይሌ  ይሁኑ ሌሎች የህዳሴው  ተዋንያን ስለ ሀገራቸው  ኪነ - ህንጻ ውበት ቢናገሩ  ምንም ዓይነት  ችግር የለውም - በጥላቻ ታውሮ  ፀጉር  ለመሰንጠቅ  ካልተፈለገ  በስተቀር፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚሰሩ ዘጋቢ ፊልሞች ውስጥም፣ እንደ አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ዓይነት ተዋቂ ሰዎችን (Celebrities) ስለ ሀገራቸው ከባቢያዊና ተጨባጭ ሁኔታዎች እንዲናገሩ ማድረግ የተለመደ አሰራር ነው፡፡ እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፣ አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ስለ ሀገሩ መናገሩ አዲሱ ነገር ምን ስለሆነ ነው ፀሐፊ ተብዬውን እንዲህ ያንጨረጨራቸው?

እርግጥ ጀግናው አትሌት የትናንት ኪነ - ህንጻ ጥበባችንን በማውሳት፣ ዛሬ ግን ከሀገር ሲወጣ " ከኢትዮጵያ ነኝ" ማለቱ ይከብዳል ብሏል፡፡ ይህ አባባሉም በአሁኑ ትውልድ ላይ ቁጭትን በመፍጠር፣ በሕዳሴው ጎዳና ይበልጥ ለልማት እንዲነሳሳ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህም በመዝገብ ቃላት ላይ የሰፈረውና የማንነታችን መገለጫ እስከ መሆን የደረሱት ድህነትና ረሃብ ጓዛቸውን ጠቅልለው ከሀገራችን መውጣታቸው ጥርጥር የለውም፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፣ የአዲስ አድማሱ "ፀሐፊ" አትሌቱን ‹ለምን ይናገራል?› ማለታቸው እንደ ማንኛውም ጭፍን ተቃዋሚ 'መንግስትን አጥላላሁ' ብለው አስበው ከሆነ የተሳሳቱ መሆናቸውን ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ግለሰቡ በተጠናወታቸው ፀረ - ሀገር አስተሳሰብ ሳቢያ 'ለምን እንደገና እናድጋለን? ፣ ለምን ድህነትና ረሃብ ከሀገራችን እንዲወጡ እናደርጋለን?' የሚል አሳፋሪ አጀንዳን እያራመዱ በመሆናቸው ነው፡፡

እንዲህ ዓይነቱ የፓርቲ ተቃዋሚነትንና የሀገርን ስር ነቀል የለውጥ እመርታን የማይለይ እንዲሁም ህዝብን ለዘለዓለሙ በተመጽዋችነት መዝገብ ላይ ለመመልከት የሚሻ ፀረ - ልማት ሰው "ኢትዮጵያዊ ነው " ብሎ ለመናገር አያስደፍርም– ለፀረ- ኢትዮጵያ ኃይሎች ተላላኪ ሆኖ የሚሰራ "ባንዳ" እንጂ፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን፣ "እንደገና" ፊልም ግለሰቡ እንደጠቀሱት የተዛባ አስተያየት ሳይሆን፣ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀና አሁን ያለውን ትውልድ ለህዳሴው ስኬት የበኩሉን ድርሻ እንዲያበረክት የሚያደርግ በጣም ጥሩ አስተማሪ መሆኑን ከላይ ከጠቀስኳቸው አብነታዊ አስረጅዎች መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በመሆኑም የግለሰቡ መረን የለቀቀ 'ለምን እናድጋለን፣ ስለምንስ እንታደሳለን?' ተቃውሞ ከጽልመታዊ ዕይታ የሚመነጭ በመሆኑ በማንኛውም ሀገር ወዳድ ዜጋ ዘንድ

ተቀባይነት የለውም፡፡ ጥቂት የጨለማ ውስጥ ዳንኪረኞች ያሻቸውን ቢለፍፉም፤ ማደጋችንና መታደሳችን አይቀርም፡፡

የተጀመረው የህዳሴ ጉዞም በእነዚህ "የወረቀት ላይ አንበሶች" የሚስተጓጎል አይደለም፡፡ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ በዘጋቢ ፊልሙ ላይ የተመለከተው ትክክለኛ አቅጣጫም የዚሁ ሃቅ መገለጫ ነው፡፡ አዎ! "እንደገና" የተሰኘው ፊልምም፤ በህዳሴው ጎዳና ውስጥ መፈጠር ያለበትን ቁጭት ያሳየና መፃዒ "እኛነታችንን" ያመላከተ ለመሆኑ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ እውነትም "እንደገና" - በህዳሴው ጎዳና!